# መናቆር የሚወዱት ፕሮፌሰር

**ሙሴ ከተክለሃይማኖት**

"ዴሞክራሲ ፣ መድብለ ፓርቲና ምርጫ በኢትዮጵያ" በሚል ርእስ የተካሄደውን የምርጫ ክርክር ተንተርሰው ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ሰሞኑን በአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ላይ "አደገኛ የአስተሳሰብ ግድፈት" እና "አነጋጋሪው የአቶ ስዩ ንግግር "በሚሉ ሁለት ርእሶች ስድብ አዘል ትችቶች መፃፋቸውን አንብቤ የበኩሌን አስተያየት ለመስጠት ተነስቻለሁ።

ፕሮፌሰሩ ትችታቸውን የጀመሩት የኢህአዴጉን ተከራካሪ ንግግር በመንተራስ ሲሆን ርዕሳቸውን ለማጠናከር ያነሱዋቸውን ጉዳዮች ለተመለከተና ላለፉት አመታት የሰውዬውን አካሄድ ልብ ብሎ ላስተዋለ የአስተሳሰብ ግድፈትና መዛባት በእጅጉ የሚስተዋልባቸው እሳቸው መሆናቸውን መረዳት አያዳግተውም ።

በመጀመሪያ ፕሮፌሰሩ ካድሬው እያሉ የጠሩት ሰው ለመግለፅ የፈለገው ብሄር ብሄረሰቦችም ሆኑ ግለሰቦች እኩል መብት ያላቸውና የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ነው። የኢህአዴጉ ተከራካሪ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ለጋራ መብቶች ትኩረት የሚሰጠውን ያህል ለግለሰብ መብቶች መከበርም ትኩረት እንደሚሰጥ በግልፅ አስቀምጠዋል።ፕሮፌሰሩ ነገር መሰንጠቅ ካልፈለጉ በስተቀር ኢህአዴግ የቡድንም ሆነ የግለሰብ መብትን አንድ ላይ አክብሮ እንደሚሄድ ጠፍቷቸው አይደለም።

የፕሮፌሰሩ አይነት የሊበራል ዴሞክራሲ አቀንቃኞች አብዮታዊ ዴሞክራሲ ለጋራ መብቶች ትኩረት የሚሰጥ በመሆኑ የጋራ መብቶች መከበር ለግለሰብ መብቶች መታፈን መሳሪያ ይሆናሉ የሚል ጭፍን መከራከሪያ ይዘው ይቀርባሉ። ይሁንና ይህ አባባላቸው በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ምንም አይነት መሰረት የሌለው ነገር ሆኖ እናገኘዋለን። ይህም በህገመንግስታችን አንቀፅ 25 ላይ #ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው፣ በመካከላቸውም ምንም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል; በሚል ያስቀምጠዋል ይህም አንዱ ማሳያ ነው።

ፕሮፌሰሩ ብሄር ብሄረሰብ የሚለው መጠሪያ ሲነሳ ህመም የሚሆንባቸው ለምን ይሆን? ዛሬ ብሄር ብሄረሰብ አትበሉ የሚሉን ፕሮፌሰር በ97ቱ ምርጫ ከብሄር ብሄረሰብም አልፈው "እናንተ ጎንደሬዎች ናችሁ፣ ጎንደሬ ደግሞ ኩሩ ነው" ወዘተ በማለት በጎጥ ሲከፋፍሉና ሲቀሰቅሱ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም።ይህም ብቻ አይደለም የአንድን ብሄር ህዝብ ከፋብሪካ ከወጣ ሳሙና ጋር ሲያመሳስሉም ተደምጠዋል።አደገኛ አስተሳሰብ ማለት ይህ ነው።የተዛባ አመለካከት ማለት ይህ ነው። የፕሮፌሰሩ አስተሳሰብ ግን ከአደገኛነቱም በላይ መርዛማነት ያለው አስተሳሰብ ነው። እንደ እኔ ለትውልድ አደጋ የሚሆነው ለብሄር ብሄረሰቦች መብት እና ልዕልና መቆምና መቆርቆር ሳይሆን የኢትዮጵያን ብሄር ብሄረሰቦች የሚያጥላላውና የሚያንቋሽሸው የፕሮፌሰሩ ንግግር ነው።

እንደሚታወቀው ፕሮፌሰሩ የአፄው ዘመን መምህር፣ደርግ ስልጣን ላይ ሲወጣ የደርጉ መርማሪና አጣሪ፣የደርግ ስርአት ሲፈርስ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ሌላ ጊዜ ደግሞ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል በመሆን በተለያዩ ስርአቶች ውስጥ ራሳቸውን እንደ እስስት ሲቀያይሩ ተስተውለዋል። ይሁንና እኝህ አቋም የለሽ ወላዋይ ፖለቲከኛ በዓላማቸው ፀንተው በመታገል ላይ ያሉ የኢህአዴግ ካድሬዎችን ለመተቸት የሞራል ብቃቱ አላቸው ብዬ አላምንም።

ፕሮፌሰሩ እንዳበደ ውሻ ይሄንንም ያንንም መልከፍ እና መናከስ ደግሞ ዋንኛ ባህሪያቸው ነው።ይህም ከስልጣን ጥማት የመነጨ መሆኑ ግልፅ ነው።ከምንም በላይ ደግሞ አሁን ባለው ስርዓት ተቀባይነት ማጣታቸው እንደሆነ ካለፈው ታሪካቸው መረዳት ይቻላል።

ኢህአዴግ የደርግን ስርአት እስከ ወዲያኛው ለመቅበር የመጨረሻውን እንቅስቀሴ በሚያደርግበት የመጨረሻዎቹ ሰአታት ወደ ኢህአዴግ አመራሮች በመሄድ "ኢትዮጵያን የማስተዳደር ስልጣን ለእኛ ስጡን፣ እኛ ሃገር ማስተዳደር እንችላለን" ብለው እንደነበር ስናስታውስ በእርግጥም ሰውዬው ለስልጣን ሲሉ የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለ እንገነዘባለን።ይህ አይነቱ ከስልጣን ጥማት የሚመነጭ

የወላዋይነት ባህሪይ በእሳቸው ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ ምሁራንም የሚስተዋል ችግር ነው።

በመጀመሪያ የደርጉ አማካሪና መርማሪ ኮሚሽን አባል ቀጥሎም ኢሰመጉ የተባለውን የፖለቲካ ፓርቲ ይሁን የሰብአዊ መብት ተሟጋች መሆኑ በውል የማይታወቅ ደርጅት መስርተው የሰብአዊ መብት ተማጋች ነኝ ሲሉ የቆዩት ፕሮፌሰሩ በሰብአዊ መብት ሽፋን የተቃውሞ ፖለቲካን ሲያራምዱ ቆይተው በ97ቱ ምርጫ አይናቸውን በጨው አጥበው የቅንጅት መስራችና አመራር ሆነው ብቅ ማለታቸው ሰውዬው በየመድረኩ ምን ያህል አቋማቸውን እንደሚቀያይሩ የሚያሳይ ነወ።

ከድጡ ወደ ማጡ እንዲሉ የቀድሞው ቅንጅት የፈረሰባቸው ፕሮፌሰር መስፍን በመቀጠል ያቋቋሙት "አንድነት"ፓርቲ ለሁለት ሲገመስና በደርዘን የሚቆጠሩ አመራሮቹ ሲባረሩ፣ ፓርቲው የውስጥ ችግሩን በውይይት መፍታት ተስኖት አንዱ ሌላውን በቆመጥ እያንጎራደደ ባደባባይ ሲያራሩጠው መምራትና ማስተባበራቸው፣ ደረታቸው ላይ የተቃውሞ መፈክር ለጥፈው መጮህና የጋዜጣ ላይ እንካሰላንቲያን መምረጣቸው ሰውዬው የአስተሳሰብ መዛባት ምንያህል እንደጎዳቸው የሚያሳይ ነው።

ለዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር ቁልፍ አስተዋፅኦ ያበረከተውንና የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት እንዲመሰርቱ ያስቻላቸውን ህገ መንግስት "ህገ አራዊት" በማለት ያጥላሉት እኚህ ሰው ዛሬም መርዘኛ ቃላትን በመርጨት ትውልድን ለማባለግ እና ወደ ጥፋት ለመምራት የሚችሉትን ሁሉ ከማድረግ አልቦዘኑም።

ፕሮፌሰር፡ አምባገነኑ መንግስቱ ሃይለማርያም በውድቀቱ ዋዜማ ወፈፍ ሲያደርገው ራሱ ከፈጠረው መዝገበ ቃላት በመነሳት "አማራ የሚባል ህዝብ የለም"የሚል ትንታኔ አቅርቦ ትዝብት ላይ እንደወደቀ ሁሉ እርስዎ ደግሞ ዛሬ በውድቀቶ ማግስት "ብሄረሰብ የሚባል ነገር የለም፣ አንድ ግራ የገባው ካድሬ የዛሬ አርባ አመት የፈጠረው ነው" ብለውናል።ፕሮፌሰሩ ብሄር ብሄረሰብ የሚለውን ያመጣው

ኢህአዴግ ነው አለማለታቸውም አንድ ነገር ነው።ፕሮፌሰሩ እንደሚጠበቡት ብሄር ብሄረሰብ  የግለሰቦች አእምሮ ፍጥረት አይደለም።ለመሆኑ በአለም ላይ ብሄር ብሄረሰብን መሰረት አድረገው የተዋቀሩ በርካታ ሃገራት እንዳሉ  እኝህ ፕሮፌሰር እንዴት ይጠፉቸዋል?

ፕሮፌሰሩ ወደዱም ጠሉም ኢትዮጵያ ያለ ብሄር ብሄረሰብ ብቻዋን ምንም እንዳልሆነች ሊያውቁ ይገባል።የብሄር ብሄረሰቦች ማንነት ባልታወቀበትና ባልተከበረበት ሁኔታ  ያለፉት ስርዓቶቻችሁ ምን አይነት ኢትዮጵያን ትተውልን እንዳለፉ እኔም እርሶም እናውቃለን።በኢትዮጵያ ለብሄር ብሄረሰቦች ቦታ ወይም እውቅና አለመስጠት ላለፉት ስርአቶች መንኮታኮት ያበረከተው አስተዋፅኦ ምን እንደሆነ አሳምረው የሚያውቁት ይመስለኛል።

የአደገኛ እና መርዛማ አስተሳሰብ ባለቤት የሆኑት ፕሮፌሰር መስፍን እንዳበደ ውሻ ያንንም ይሄንንም ከመናከስ በቀር ለዚህች ሃገርና ህዝብ ጥቅምም ሆነ ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መጎልበት ያበረከቱት አስተዋፅኦ ምን አለ? ሌላው ቢቀር የነገ ሃገር ገንቢ የሆኑትን ታዳጊ ወጣቶችን ንፁህ አእምሮ  መመረዝን ስራዬ ብለው መያያዝዎትን ቢያቆሙ  እንኳ ምንኛ መልካም ነበር። ሲሆን ሲሆን ከእርስዎ መሰል ምሁራን ይህቺ አገር የምትጠብቀው መልካም ተግባርን ነበር።

ሌላው ፕሮፌሰሩን ክፉኛ የከነከናቸውና የአስተሳሰብ መዛባት በማለት ለመተቸት የሞከሩት አቶ ሴኮቱሬ  የሰጡትን አስተያየት ነው። አቶ ሴኮቱሬ “አቶስዬ ያንን የፌውዳል ስርአት ከናፈቁ አመለካከታቸው 35 አመት ወደሁዋላ መቅረቱን ከማመላከቱ በቀር ሌላ ትርጉም አይሰጥም” ማለታቸው ምኑ ላይ ነው የተዛባ አስተሳሰብ  የሚያስብለው? አሁንስ ቢሆን የፌውዳሉን የምርጫ ስርአት ማድነቅ ኋላ ቀርነት አይደለም ከተባለ ምን ሊባል ይችላል ? የተዛባ አስተሳሰብ የያዙት ፕሮፌሰር መስፍን እና አቶ ስዬ እንጂ ማን ሊሆን ይችላል?

ይሁንና ፕሮፌሰሩ በአቶ ስዬ ላይ የተሰጠው አስተያየት እንዳልከነከናቸው በሁለተኛው ፅሁፋቸው ላይ “እኔ ከተሸነፍኩ ምርጫው ተጭበርብሯል” የሚለውን

የአቶ ስዬን ንግግር ሲያብጠለጥሉ ተስተውለዋል።ለመሆኑ ይህ የአቶ ስዬ አባባል ከማን የተወረሰ ሆኖ ነው ፕሮፌሰሩን እንዲህ ያንገበገባቸው? “በምንም ተአምር እኔን ወይም እኛን የሚያሸንፍ ተወዳዳሪ የለም” የሚለው ግብዝነት የተሞላበት ንግግር እነ ፕሮፌሰር መስፍን ሲመሩት የነበረው ቅንጅት የ97ቱ ምርጫው ከመካሄዱ በፊት ሲለው የነበረና በኋላም ለአመፅ ማቀጣጠያነት ሲጠቀምበት የነበረ መሆኑን ዘንግተውት ይሆን?

እኚህ ሰው ባለፉት ስርአቶች ለሃገራቸው ያበረከቱት አዎንታዊ አስተዋፅኦ ስለመኖር ወይም ስላለመኖሩ አላውቅም። ነገር ግን አሁን ላለውም ሆነ ለቀጣዩ ትውልድ የሚያበረክቱት በጎ አስተዋፅኦ ካለመታየቱም በላይ ከጥቅማቸው ጉዳታቸው ያመዘነ ሆኖ ይታየኛል።

ዛሬ የቀድሞ አጋሮቻቸው ጭምር አንቅረው የተፏቸው እኚህ ሰው እንደ እድሜ ጠገብነታቸውና አንጋፋ ምሁርነታቸው ለሃገራቸውና ህዝባቸው ሊያበረክቱት የሚገባ በጎ አስተዋፅኦ ቢኖርም እሳቸው የመረጡት አካሄድ ግን ከሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ይልቅ የከተማ ነፃ ትግልን መምራትና ማስተባበር ነው። በተጨማሪም ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ በየጋዜጣው ሰውን ለመዝለፍ እቅድ ያወጡ እስኪመስልባቸው ድረስ ነገር በመሰንጠቅና ይህንንም ያንንም በመዝለፍ መጠመዳቸው “ካረጁ አይበጁ” የሚለውን የአበው ብሂል በእጅጉ የሚያረጋግጥ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። በመሆኑም አሁንም ወደ ትክክለኛው ህሊናቸው ተመልሰው ለዚህች አገር በጎ አስተዋፅኦ ቢያበረክቱ ለራሳቸውም ሆነ ለአገራቸው ይጠቅማል። እምቢ ካሉ ግን የኡኡታ ፖለቲካው እየመሸበት በመምጣቱ ሰሚ እያጡ መምጣታቸውን ይወቁት እላለሁ።